DISTRICT OF COLUMBIA PUBLIC SCHOOLS

GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA MURIEL BOWSER, MAYOR

# የአዕምሮ ጤና - የመረጃ-ምንጭ መምሪያ/Guide

## የትምህርት ዓመት 2025-2026

በዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ውስጥ፣ የአዕምሮ ጤና - የመረጃ-ምንጮችን ለማግኘት-የሚረዳችሁ መምሪያ/guide።



**DCPSMENTALHEALTH.ORG**

school.mentalhealth@k12.dc.gov



**የእኛ ማንነት**

# የእኛ ማንነት

የዲሲየሕዝብ ትምህርት ቤቶች (DCPS) - የትምህርት ቤት የአዕምሮ ጤና/School Mental Health (SMH) ቡድን፣ትምህርት ቤቶችን ለማገልገል በትጋት-የሚሰራ እና የእያንዳንዱን ልጅ አጠቃላይ-የሆነ ደህንነት የሚደግፍ-ነው። ሙያዊ-እውቀት-ያላቸው ቡድናችን፣ ሁሉን-አቀፍ የሆነ ማማከርን እና አገልግሎቶችን - በደንብ-በተረጋገጠ የግምገማ-ማድረጊያ ዘዴዎች እና ቴራፒያዊ-የሆነ ልምዶችን በመጠቀም - አገልግሎት ይሰጣሉ። የተማሪዎችን በየግል-የሚያስፈልጓቸውን-ነገሮች በቅድሚያ ለይቶ-በማወቅ፣ ስኬታቸውን የሚያረጋግጥ - ለእነሱ-የተዘጋጀውን እርዳታ እንሰጣለን። በማስረጃ-ላይ መሠረት ያደረገው አቀራረባችን ሊያመጣ-ከሚችለው ለውጥ፣ የተሞክሮ-ልምድ አግኙ።

# የቀውስ/Crisis - የእርዳታ ቁጥሮች

በአዕምሮ ጤና ቀውስ ውስጥ፣ ትክክለኛውን እርዳታ ማግኛ-መንገድን ማወቅ - ወሳኝ-ነገር ነው። ዝግጁ-አድርጋችሁ ልታስቀምጡት የሚገባችሁን፣ ጠቃሚ-የሆኑ የማግኛ ስልክ-ቁጥሮችን ዝርዝር - በአንድ-ላይ አዘጋጅተናል። እናንተ ወይም እናንተ-የምታውቁት ሰው፣ ወዲያው-እርዳታ በሚያስፈልገው-ጊዜ፣ የት-መሄድ እንዳለባችሁ በማወቅ እና ዝግጅት-አድርጋችሁ ቆዩ። በአስቸኳይ የአደጋ-ሁኔታዎች ሲኖሩ፣ 9-1-1 መደወልን - አስታውሱ።

**የልጅ እና የጎረምሳ - የሞባይል ሳይካትሪክ አገልግሎት/Child and Adolescent Mobile Psychiatric Service (ChAMPS)**፧ የአዕምሮ ጤና ወይም የባህሪያዊ የጤና ቀውስ ላላቸው - ልጆች፣ ታዳጊ-ወጣቶች፣ እና ጎረምሳ አዋቂዎች የሚሰጥ የአስቸኳይ-ጊዜ ምላሽ-አሰጣጥ አገልግሎት ነው።

**202-481-1440**

**በዲሲ የባህሪይ ጤና መምሪያ/DC Department of Behavioral Health ውስጥ፣ የእርዳታ-መስመር (Helpline)ን ማግኘት**፧ በቀን ለ24-ሰዓት፣ በሣምንት-ለሰባት-ቀን አገልግሎት-የሚሰጥ የስልክ መስመር ሲሆን፧ በባህሪያዊ ጤና ላይ ባለሞያተኞች-በሆኑ ሠራተኞች የተሞላ እና ስልክ-ደዋዩ ወዲያውኑ እርዳታ ወይም ቀጣይነት-ያለው እንክብካቤ እንዲያገኝ - ለመምራት/refer-ለማድረግ የሚችሉ ናቸው።

**1-888-7WE-HELP**

**የዋሽንግተን የሳይካትሪክ ተቋም/The Psychiatric Institute of Washington (PIW)**፧ የአዕምሮ ጤና እና የአደንዛዥ-ዕፅን አለአግባብ-መጠቀም ጉዳዮች ለገጠሟቸው - ልጆች፣ ጎረምሶች እና አዋቂዎች፣ ሁሉን-አቀፍ የሆነ የባህሪያዊ ጤና-እንክብካቤን ይሰጣል።

**1-800-369-2273**

**የራስን-ሕይወት የማጥፋት & የቀውስ ነፍስ-ማዳኛ/Suicide & Crisis Lifeline**፧ የ24-ሰዓት፣ ሚስጢራዊነትን-የጠበቀ እርዳታን - ለማንኛውም የራስን-ሕይወት ለማጥፋት ቀውስ-ውስጥ ለሚገኝ ወይም ስሜታዊ-ጭንቀት ውስጥ ለሚገኙ እርዳታ-ይሰጣል። ስልጠና-ካላቸው የቀውስ-ካውንስለር/crisis counselor ጋር ለመነጋገር፣ ደውሉ ወይም ቴክስት/text አድርጉ።

**Call or text 988**

# ስለ ተማሪው፣ ስጋት አላችሁ?

የምታውቁት ተማሪ - የአዕምሮ-ጤና ፈታኝና-አስቸጋሪ ሁኔታዎች እየገጠሙት ከሆነ፣ ይህን የመመራት/**referral** ቅጽን እባካችሁ ሞታችሁ አጠናቅቁ - እና የትምህርት ቤት የጤናማነት ቡድን አባል - ምላሽ-ይሰጣል።

## እዚህ ስካን/SCAN አድርጉ

**የአዕምሮ-ጤናን መታደግ፣ ግድ-ይለናል።**

**እኛ - እዚህ ያለነው፣ ለእናንተ ነው።**



# የአዕምሮ ጤና አጋሮች/Mental Health Partners

በትምህርት ቤት ውስጥ - ሁሉም ተማሪዎች የሚያስፈልጓቸውን እርዳታዎች ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ፣ DCPS - ትምህርት ቤቶችን በማህበረሰብ-ላይ መሠረት ካደረጉ ድርጅቶች (Community-Based Organizations (CBOs) ጋር በማጣመር - የአዕምሮ ጤና አገልግሎቶችን ለማስፋፋት የሚረዳ ተነሳሽነትን አስጀምሯል። የDCPS ትምህርት ቤት የአዕምሮ ጤና (Mental Health) ቡድን፤ ከእነዚህ 'CBO'ዎች ጋር አጋር-በመሆን፣ በሁሉም በሦስት ዘርፍ ጠንካራ-አገልግሎቶች/three tiers of intensity ውስጥ፣ ተጨማሪ አገልግሎቶችን ለመስጠት አጋርነትን-ፈጥረዋል።

አንዳንድ የ'CBO' አጋሮች - ሌላ ጠንከር-ብለው የሚሰጡ አገልግሎቶችንም - የሚከተሉትን-ጨምሮ ነገር-ግን በእነዚህ ብቻ ሳይወሰን፣ ይሰጣሉ:

- የቤተሰብ ተግባራዊ-የሆነ ቴራፒ/Family functional therapy
- አሰቃቂ-ጉዳት-ላይ ያተኮረ የግንዛቤ የባህሪይ ቴራፒ/Trauma-focused cognitive behavior therapy
- የወላጅ-ልጅ የእርስ-በርስ ግንኙነት ቴራፒ/Parent-child interaction therapy
- ባለብዙ-ስርዓት ቴራፒ/Multi-systemic therapy
- አደንዛዥ-ዕፅን መጠቀም/Substance use
- በንቃት-የማሰብ ስልጠና/Mindfulness training

ሌሎች 'CBO'ዎች፤ ከትምህርት ቤት ውስጥ መሠረት ካደረገ የአዕምሮ ጤና አገልግሎቶች ባለፈ-ሁኔታ - የሳይካትሪክ/psychiatric አገልግሎቶችን እና በማህበረሰብ-ላይ መሠረት ያደረጉ እርዳታዎችን ይሰጣሉ።

ተደጋግመው የሚጠየቁ ጥያቄዎች (Frequently Asked Questions)

# F.A.Q

## በትምህርት ቤት-መሠረት ያደረገ የአዕምሮ ጤና አገልግሎቶች፣ ምንድን-ናቸው?

በትምህርት ቤት ላይ መሠረት ያደረገ የአዕምሮ ጤና አገልግሎቶች፤ ለተማሪዎች፣ በልጁ አጠቅላይ ዕድገት ላይ ትኩረት በሚያደርጉ፣ ብቁ-በሆኑ የትምህርት ቤት ሠራተኞች - የሚሰጡ ናቸው። እነዚህ አገልግሎቶች፤ ተማሪያችሁ ያላቸውን በርካታ-የሆኑ የሚያስፈልጓቸውን-ነገሮች - ከቀለም-ትምህርት አስቸጋሪና-ፈታኝ ነገሮች እስከ ሐዘን ያሉትን እና፣ በሞት-መለየት/loss፣ ጭንቀት፣ አሰቃቂ-ጉዳት/trauma እና ሌሎች ታዳጊ-ሰዎች ለሚጋፈጧቸው አስቸጋሪና-ፈታኝ ለሆኑ-ነገሮች ምላሽ-መስጠት ይችላሉ።

## በትምህርት ቤት-መሠረት ያደረገ የአዕምሮ ጤና አገልግሎቶች፣ ማን ይሰጣል?

እነዚህ አገልግሎቶች፤ በአዕምሮ ጤና ባለሞያተኞች እና በትምህርት ቤት ካውንስለሮች - ይሰጣሉ።

- የDCPS በትምህርት ቤት-መሠረት ያደረጉ የአዕምሮ ጤና ባለሞያተኞች፤ ሁሉም በየስቴት የትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ቢሮ (Office of State Superintendent of Education (OSSE) ሰርቲፋይ-የሆኑ ናቸው።
- የትምህርት ቤት ማህበራዊ ሠራተኞች (social workers)፣ በጤና-ባለሞያነት ደረጃ በዲሲ ጤና/DC Health - ፈቃድ-ያገኙም ናቸው።
- ከዲሲ የባህሪይ ጤና መምሪያ (DC Department of Behavioral Health's (DBH) በትምህርት ቤት-ላይ መሠረት ያደረገ የባህሪያዊ ጤና ፕሮግራም/School-Based Behavioral Health Program እና ከእኛ በማህበረሰብ-ላይ መሠረት ያደረጉ ድርጅቶች (Community-Based Organizations (CBOs) የመጡ የጤና-ባለሞያተኞች፤ በየግላቸው ፈቃድ-ያላቸው ወይም-ደግሞ ኤጀንሲው በ'DBH' እና በ'DCPS' በፀደቀው - ፈቃድ-ባለው ባለሞያተኛ ቁጥጥር-የሚደረግባቸው ናቸው።

ተደጋግመው የሚጠየቁ ጥያቄዎች (Frequently Asked Questions)

# F.A.Q

## በትምህርት ቤት ካውንስለር፣ የትምህርት ቤት የስነልቦና ባለሞያተኛ/school psychologist እና በትምህርት ቤት ማህበራዊ ሠራተኛ/school social worker መካከል-ያለው ልዩነት ምንድነው?

የትምህርት ቤት ካውንስለሮች፣ የስነልቦና ባለሞያተኞች፣ እና የማህበራዊ ሠራተኞች - እያንዳንዳቸው በሁሉም ዕድሜዎች ውስጥ ለሚገኙ ተማሪዎች ስሜታዊ ጤናን በመደገፍ-ላይ፣ ወሳኝ-የሆነ ሚናን-ይጫወታሉ። እያንዳንዱ ባለሞያተኛ ቡድን፣ የተለያየ - ነገር-ግን ወሳኝ-የሆነ ሚናዎችን - ለተማሪዎች ውጤቶችን ለማስገኘት እና በትምህርት ቤት ማህበረሰቦች ውስጥ በመርዳት ይሠራሉ።

**የትምህርት ቤት ካውንስለሮች/School counselors** ተማሪዎችን በቀጥታ - በቀለም-ትምህርት ዕቅድ-አወጣጥ እና ግቦችን-በማስቀመጥ፣ የተማሪን ስኬት በሚያሳድገው በመማሪያ-ክፍል ትምህርቶች ላይ፣ እና ተማሪዎች ከክፍል-ወደክፍል በሚሸጋገሩበት ጊዜ - በአነስተኛ-ቡድን (small-group) ጣልቃ-ገብነቶች በመርዳት ይሠራሉ። በሁለተኛ-ደረጃ ላይ፣ ተማሪዎች ለከፍተኛ-ደረጃ ትምህርት፣ በውትድርና/military ወይም በስራ-መስክ ላይ እንዲያቅዱ በመርዳትም-ይሰራሉ። በተጨማሪም - በትምህርት-ቤት አቀፍ የመከላከያ ፕሮግራም-አሰጣጥ ውስጥ አስተዋጽዖ የሚያደርጉ እና በትምህርት ቤት ውስጥ እንደ-የሚታመኑ አዋቂዎች/trusted adults ሆነው ያገለግላሉ።

**የትምህርት ቤት የስነልቦና-ባለሞያተኞች/School Psychologists**፤ ትምህርት-ሰጪዎች - የተማሪውን ጠንካራ-ጎኖች ለመለየት እንዲችሉ እና በሁለቱም በቀለም-ትምህርት እና በማህበራዊ-ስሜታዊነት ዙሪያ በሚያሳዩት ዕድገት-ዙሪያ ለማወቅ ይረዳቸዋል። በትምህርት ቤት ውስጥ በሚከናወነው - በባለ-ብዙ ዘዴዎች (Multi-Tiered System of Supports (MTSS) ስራ ውስጥ እንደ መሪዎች-ሆነው አገልግሎት-የሚሰጡም ሲሆን፣ በአካዳሚክ፣ በማህበራዊ-ስሜታዊነት፣ ከትምህርት-ገበታ ጋር በተያያዘ፣ ወይም ባህሪያዊ-ሁኔታም ቢሆንም-ባይሆን - በእነዚህ ዙሪያ ያሉትን አስቸጋሪና-ፈታኝ ነገሮችን ለማሻሻል፣ የችሎታ ጉድለቶችን ለመለየት እና ለመደገፍ፣ አጋርነትን-ይፈጣሉ። የትምህርት ቤት የስነልቦና-ባለሞያተኞች/School Psychologists - በተጨማሪም፣ የጉዳተኝነትን ቀደም-ያሉ ምልክቶችን የሚያሳዩ ተማሪዎች በመመርመር እና ተማሪዎች የሚያስፈልጋቸውን የእርዳታ-መጠን ለመወሰን የመረጃ-ስብስብ (data) ይሰበስባሉ። አስጊ-የሆኑ ጉዳዮች ተደጋግመው-ከተከሰቱ፣ የትምህርት ቤት የስነልቦና-ባለሞያተኞች - ለጉዳተኝነት ምደባ/disability classification፣ ተማሪው የብቁነት መስፈርትን ያሟላ-እንደሆነ፣ እና የልዩ-ትምህርት አሰጣጥን እና/ወይም ተዛማጅ የሆኑ አገልግሎቶች (related services)ን ማግኘት-ያስፈልገው እንደሆነና-እንዳልሆነ ለመወሰን እንዲረዳ፣ ሁሉን-አቀፍ የሆነ የስነልቦና ግምገማዎችን ያጠናቅቃሉ። የትምህርት ቤት የስነልቦና-ባለሞያተኞች፤ ለትምህርት ቤት አቀፍ የአዕምሮ ጤና መከላከል እቅድ-አወጣጥ እና አፈፃፀም - አስተዋጽዖ ያደርጋሉ።

**የትምህርት ቤት ማህበራዊ ሠራተኞች/School social workers**፤ በሁለቱም - በዲሲ የጤና መምሪያ (DC Department of Health) እና በ‘OSSE’፣ ፈቃድ-ያገኙ ናቸው። በማስረጃ-ላይ መሠረት ያደረገ የአዕምሮ ጤና ህክምናዎችን እና ልምምዶችን - ለተማሪዎች ለመስጠት፣ ስልጠና-ያላቸው ናቸው። የትምህርት ቤት ማህበራዊ ሠራተኞች (School social workers)፣ በተማሪው የየግል የትምህርት ዕቅድ (Individualized Education Plan (IEP)፣ ‘504 plan’፣ እና ተሟልቶ-የተጠናቀቀውን ተግባራዊ ባህሪያዊ ግምገማዎች (Functional Behavior Assessments (FBA) እና የባህሪይ ጣልቃ-ገብነት ዕቅዶች (Behavior Intervention Plans (BIP) ውስጥ በተካተቱት-መሠረት፤ የባህሪይ የድጋፍ አገልግሎቶችን ለመስጠት በጣም ተስማሚ-የሆኑ ናቸው።

ተደጋግመው የሚጠየቁ ጥያቄዎች (Frequently Asked Questions)

# F.A.Q

### በማህበረሰብ-ላይ መሠረት ያደረገ ድርጅት (Community-based Organization (CBO) የጤና-ባለሞያተኞች - እንደ-በትምህርት ቤት-መሠረት ያደረገ የአዕምሮ ጤና አቅራቢዎች (school-based mental health providers) - አንድ-ዓይነት የሆኑ ናቸው?

የ‘CBO’ የጤና-ባለሞያተኞች/clinicians፤ በየራሳቸው ኤጀንሲዎች ተቀጥረው-የሚሰሩ፣ የDCPS ተቀጣሪ-ሠራተኞች ያልሆኑ ናቸው። ተማሪዎችን እና ቤተሰቦችን ለመርዳት፣ ከDCPS በትምህርት ቤት-መሠረት ካደረጉ የአዕምሮ ጤና አገልግሎት-ሰጪዎች ጎን-ለጎን ሆነው ይሰራሉ። ሁለቱም የባለሞያተኞች ቡድኖች - ለተማሪዎች እና ቤተሰቦች፣ እርዳታ-ሰጪ አገልግሎቶችን ያቀርባሉ። የ‘CBO’ የጤና-ባለሞያተኞች/clinicians - ሆኖም-ግን፣ በ‘IEP’ ወይም ‘504 plan’ ላይ አገልግሎቱ-እንዲሰጥ ለተደረገላቸው ተማሪዎች - የባህሪይ እርዳታ አገልግሎቶችን አይሰጡም።

### ልጄ፣ ወደ ‘CBO’ የተመራው/referred-የሆነው፤ ለምንድነው?

ተማሪዎች - ወደ ‘CBO’ዎች በትምህርት ቤት ባለ-ብዙ ዘርፍ የእርዳታዎች ዘዴ (Multi-Tiered System of Supports (MTSS) አማካኝነት ይመራሉ/referred-ይሆናሉ። ትምህርት ቤቶች፤ የመረጃ-ስብስብ (data)ን በተማሪ የዕድገት-ሂደት ላይ - በተለያዩ-ነገሮች ዙሪያ: በንባብ፣ በሂሳብ፣ በትምህርት-ገበታ ላይ በመገኘት (attendance)፣ እና በባህሪይ ላይ-ለመመልከት ጥቅም-ላይ ያውሉታል። እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች፤ እርዳታ በሚያስፈልጓቸው ነገሮች ዙሪያ - ዒላማ-ያደረገ ጣልቃ-ገብነቶች ይሰጣቸዋል። በትምህርት ቤት-መሠረት ያደረገ የአዕምሮ ጤና (Mental Health) ቡድን እና አጋሮች፤ የየግል የተማሪዎችን ፍላጎቶች ለማሟላት፣ ተመራጭ-የሆነውን የጤና-እገዛ እና/ወይም ድርጅት - ለመወሰን፣ በአንድነት-ሆነው ይሰራሉ።

### ከ‘CBO’ ለተማሪዬ ከሚሰጠው አገልግሎቶች ጋር ተያያዥ-የሆነ ክፍያ አለ?

ኢንሹራንስ ያላቸውም-ሆነ የሌላቸው፣ ማንም-ተማሪ አገልግሎቶችን ከማግኘት አይከለከልም። ሆኖም-ግን፣ ተማሪው ተቀባይነት-ባለው ኩባንያ አማካኝነት፣ ኢንሹራንስ ካለው፤ ለአገልግሎቶቹ - ኢንሹራንሱ እንዲከፍት የማስከፈያ-ጥያቄ ይደርሰዋል። የማስከፈያ አገልግሎቶች (Billing for services)፣ የ‘CBO’ የጤና-ባለሞያተኞች - ዘርፍ 3/Tier 3 አገልግሎቶችን በትምህርት ቤት አቀማመጥ-ውስጥ ለመስጠት እንዲችሉ-ያደርጋቸዋል። የጤና-ባለሞያተኞች፣ የጤና ኢንሹራንስ መረጃን - ለማስከፈያ-ሂደት ብቻ ሲባል - ይጠይቃሉ። ኢንሹራንስ የሌላቸው ተማሪዎች፣ ከ‘CBO’ የጤና-ባለሞያተኛ ጋር በመሆን ኢንሹራንስ ለማግኘት ወይም ከDCPS ትምህርት ቤት የአዕምሮ ጤና አገልግሎት-አቅራቢ ወይም ካውንስለር - እንደየ-ሚያስፈልጋቸው ደረጃ-መጠን መሠረት-አድርጎ እርዳታ-ለማግኘት መስራት-ይችላሉ።

### ልጄ - የተማሪ እራስን-የመምራት ቅጽ/Student Self-Referral Formን ከሞላ፣ ወይም ለአዕምሮ-ጤና አገልግሎቶች በሌላ አዋቂ ከተመራ/refer-ከተደረገ፤ እኔ-እንዳውቅ ይደረጋል?

በሕጉ-መሠረት፣ ተማሪዎች - የወላጅ ስምምነት ሳይኖር - የአዕምሮ ጤና አገልግሎቶችን ማግኘት ይችላሉ። ሆኖም-ግን፣ DCPS ወላጆችን እንደ አጋሮች-አድርጎ ስለሚያይ፣ እና ዲስትሪክቱ ወላጆችን በመምራት/referral ሂደት ውስጥ ስለሚያካትት፣ ስምምነታቸውን በተቻለ-መጠን ማግኘትን-ይፈልጋል።

### የማማከር-አገልግሎት (counseling)/የባህሪያዊ እርዳታ አገልግሎቶችን - ከሌላ-የውጪ ኤጀንሲ ቀድሞውኑ-የሚያገኙ ከሆነ፣ ልጄ አገልግሎቶቹን በትምህርት ቤት ውስጥ ማግኘት-ይችላል?

አዎን/Yes። ልጃችሁ ከውጪ-ኤጀንሲ አገልግሎቶችን የሚያገኝ ከሆነ፣ በትምህርት ቤት መሠረት-ያደረገ የአዕምሮ ጤና አገልግሎቶችንም - ሊያገኙ-ይችላሉ። አገልግሎቶች እና ህክምናው በአንድ-ላይ ሊጣመር እንዲችል-ለማድረግ ሲባል፣ ይህ መረጃ - ከልጃችሁ የውጪ-አገልግሎት ሰጪ ጋር መጋራቱ-ሊረዳ የሚችል-ይሆናል።

### ልጄ - የ‘CBO’ የጤና-ባለሞያተኛን የሚያይ-ከሆነ፣ ከDCPS ጋር የሚጋራ የህክምና-መረጃ አለ?

የለም/No፤ ግን DCPS - ተማሪዎቻችን በሕክምናው እድገት-እያመጡ መሆንና-አለመሆናቸውን የማወቅ-ፍላጎት አለው። በትምህርታዊ ዕቅድ-አወጣት እና የእድገት-ሂደት መቆጣጠሪያ ይዘት-ውስጥ ያሉት - መሠረታዊ-የሆነ የእድገት-ሂደት፣ ሊጋራ-ይችል ይሆናል። ለDCPS የተሰጠው - መደበኛ-የዘወትር መረጃዎች - የሚከተሉት ነው:

- የተማሪው የጤና-ባለሞያ/clinician - ስም
- የጤና-ባለሞያው - ያለው-ፈቃድ ሁኔታ/Clinician’s licensure status
- የጤና ባለሞያ ተቆጣጣሪው ስም እና የፈቃድ ሁኔታ፤ በራሳቸው ለመስራት ፈቃድ-የሌላቸው ከሆነ

# የDCPS የአዕምሮ ጤና - ድህረ-ገጽ

የDCPS የአዕምሮ ጤና ድህረ-ገጽ፣ ድጋፍ-ሰጪ የሆነ እና ለተጠቃሚዎች ቀላል-የሆነ የመረጃ-ምንጭ ሲሆን - በተለይ-ደግሞ ወላጆችን በአዕምሮአችን-ውስጥ በማድረግ - ዲዛይን የተደረገ ነው። የመረጃ-ምንጮቹ ጠንካራ-የሆነ የአዕምሮ ጤናማነትን ለማስፋፋት-እንዲችል፣ የአካባቢያችሁ የትምህርት ቤት የአዕምሮ ጤና ቡድኖች ማውጫ/directoryእና አውደ-ጥናቶችን፣ ዌቢናሮችን እና የማህበረሰብ እንቅስቃሴዎችን - የሚያሳየውን፣ የዝግጅቶች የቀን-መቁጠሪ/events calendarን - በ**dcpsmentalhealth.org**. ላይ ጎብኙ።



# የአገልግሎት-ሰጪ - ማውጫ/Provider Directory



የትምህርት ቤት የአዕምሮ ጤና አገልግሎት-ሰጪ ማውጫ/Provider Directory፣ ጠቃሚ-የሆነ የመረጃ-ምንጭ ሲሆን፣ በDCPS የአዕምሮ ጤና ድህረ-ገጽ ላይ ይገኛል። የትምህርት ቤት የስነልቦና-ባለሞያተኞችን፣ ማህበራዊ-ሠራተኞች (Social Workers)ን፣ የትምህርት ቤት ካውንስለሮች/Counselorsን፣ እና በማህበረሰብ-ላይ መሠረት ያደረጉ ድርጅቶችን - በDCPS ዙሪያ፣ አግኙ።

**‘ማውጫ/Directory’**ን ተመልከቱ